# ዜና አመዝኤ





## በጎርፍ አደጋ ለተጎዱ ወገኖች መርጃ ከብር 50 ሚለዮን በላይ ተለግሷል

### ህዳር 24 ቀን 1999 ዓ.ም በተካሔደው የቴሌቶን ዝግጅት ብር 30 ሚሊዮን ያህል ቃል ተገብቷል።

በጎርፍ አደጋ ለተጎዱ ወገኖቻችን መርጃ ከሀገር ውስጥ የተለያዩ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና ሠራተኞቻቸው ፣ የልማት ድርጅቶች ፣ የክልል መንግስታት ፣ ማህበራት ፣ ዕድሮች ፣ የሀይማኖት ተቋማት እና ግለሰቦች ፣ ከሀገር ውጭ ደግሞ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያ ወዳጆች ፣ የውጭ መንግስታት እና ዓለም አቀፍ ለጋሽ ድርጅቶች እስከ ህዳር 22 ቀን 1999 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ በጠቅላላው ብር 50 ሚሊዮን 326 ሺህ 147 ከ20 ለግሰዋል።



ከዚሁ እስከ ህዳር 22 ቀን 1999 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ ከተለገሠው ዕርዳታ ውስጥ ብር 39 ሚለዮን 519 ሺህ 391 ከ06 በጥ ገንዘብ የተለገሰ ሲሆን ቀሪው ብር 10 ሚለዮን 806 ሺህ 756 ከ14 ሳንቲም ደግሞ በአይነት የተለገሰ መሆኑን ከአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ የዕርዳታ ማሰባሰብ ቡድን የተገኘው መረጃ ያመለክታል።

በጎርፍ አደጋ ለተጎዱ ወገኖቻችን በተለያዩ የህብረተሰቡ ክፍሎች በጥሬ ገንዘብና በአይነት የሚለገሠው ዕርዳታ በማዕከል እና በድሬዳዋ አስተዳደር ካውንስል አማካይነት የሚሰባሰብ ነው።

በዚሁ መሠረት እስከ ህዳር 22 ቀን 1999 ዓ.ም በጥሬ ገንዘብ ከተለገሰው ጠቅላላ ብር 39 ሚሊዮን 519 ሺህ 391 ከ06 ውስጥ ብር 30 ሚሊዮን 317 ሺህ 841 ከ38 በማዕከል ቀሪው ብር 9 ሚሊዮን 201 ሺህ 549 ከ68 በድሬዳዋ አስተዳደር ካውንስል የተሰባሰበ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል።

በተመሳሳይም እስከተጠቀሰው ጊዜ ድረስ በአይነት ከተለገሰው ጠቅላላ ብር 10 ሚሊዮን 806 ሺህ 756 ከ14 ሳንቲም ውስጥ ብር 6 ሚሊዮን 206 ሺህ 756 ከ14 የሚሆነው በማዕከል ቀሪው ብር 4 ሚሊዮን 600 ሺህ የሚሆነው ደግሞ በድሬዳዋ አስተዳደር ካውንስል የተሰባሰበ

በዚህ ዕትም ውስጥ

ለህዳር ወር ከ 100 ሺህ ኩንታል በላይ የምግብ ዕርዳታ ተመድቧል
*ገጽ 2*

በትራንስፖርትና በመንገድ ብልሽት ምክንያት የዘገየው ዕርዳታ መከፋፈል ጀመረ
*ገጽ 3*

በሱማሌ ክልል ለጎርፍ አደጋ ተጎጂዎች የዓለም ምግብ ኘሮግራም ሄሊኮኘተሮች ዕርዳታ በማቅረብ ላይ ይገኛሉ
*ገጽ 4*

በመኸር አምራች እና በአርብቶ አደሩ አካባቢዎች የምግብ ዋስትናን ሁኔታ የሚያጠኑ ቡድኖች ተሠማርተዋል
*ገጽ 5*

በአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ ህዝብ ግንኙነት የሚዘጋጅ
ስልክ. 5529259
ጠ.ሳ.ቁ 5686
ድረገጽ፣ www.dppc.gov.et

መሆኑን የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡

ይኸ በዚህ እንዳለም በጎርፍ አደጋ ለተጎዱ ወገኖቻችን መልሶ ማቋቋሚያ ዕርዳታ ማሰባሰቢያ ህዳር 24 ቀን 1999 ዓ.ም በተካሔደው የቴሌቶን ዝግጅት ብር 30 ሚሊዮን ያህል ቃል ተገብቷል፡፡

በዚሁ ክቡር ኘሬዝዳንት ግርማ ወ/ጊዮርጊስ እና ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ በአጠቃላይ ልዩ ልዩ የህብረተሰቡ ክፍሎች ብር 30 ሚሊዮን ያህል ለመለገሥ ቃል ገብተዋል፡፡

በዚህ የቴሌቶን ዝግጅት መላው ህዝብና የተለያዩ የህብረተሰቡ ክፍሎች በንቃት የተሳተፉበትና ህዝቡ ለወገን ደራሽነቱን በድጋሚ ያሳየበት አበረታች ዝግጅት መሆኑን የገለጹት የአመዝኤ ዋና ዳይሬክተር አቶ ሲሞን መቻለ የድንገተኛ አደጋ ሠለባ



ክቡር ኘሬዝዳንት ግርማ ወ/ጊዮርጊስ እና ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ በተገኙበት በሸራተን አዲስ ሆቴል በተካሔደው የቴሌቶንና ምሣ ዝግጅት ላይ የአውሮፖ ህብረት ቃል የገባውን ብር 70 ሚሊዮን ሳይጨምር ከሀገር ውስጥ የተለያዩ የመንግስትና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ ማህበራት ፣ የንግድ ተቋማት ፣ የሀይማኖት ተቋማት እና ግለሠቦች በአጠ ቃላይ ልዩ ልዩ የህብረተሰቡ ክፍሎች ብር 30 ሚሊዮን ያህል ለመለገሥ ቃል ገብተዋል፡፡

በተገኙበት በሸራተን አዲስ ሆቴል በተካሔደው የቴሌቶንና ምሣ ዝግጅት ላይ የአውሮፖ ህብረት ቃል የገባውን ብር 70 ሚሊዮን ሳይጨምር ከሀገር ውስጥ የተለያዩ የመንግስትና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ ማህበራት ፣ የንግድ ተቋማት ፣ የሀይማኖት ተቋማት እና ግለሠቦች የሆኑ ወገኖችን ለመርዳት ቃል የገቡ ወገኖች ሁሉ ቃል የገቡትን የገንዘብ መጠን በተቻለ መጠን በቶሎ በመስጠት ለተግባር ሥራው መፋጠንም የበኩላቸውን አስተዋጽኦ የደርጋሉ የሚል እምነት እንዳላቸው በዝግጅቱ መዝጊያ ላይ ባሰሙት ንግግር ገልፀዋል፡፡

## ለህዳር ወር ከ 100 ሺህ ኩንታል በላይ የምግብ ዕርዳታ ተመድቧል

በተለያዩ ክልሎች በደረሱ የተፈጥሮ አደጋዎች ሳቢያ የአስቸኳይ ጊዜ ዕርዳታ ለሚያስፈልጋቸው ወገኖች ለህዳር ወር በጠ ቅላላው 100 ሺህ 877.1 ኩንታል የምግብ ዕርዳታ ተመድቧል፡፡

ከዚህ ለወሩ ከተመደበው ጠቅላላ የምግብ ዕርዳታ ውስጥ 98 ሺህ 700 ኩንታል በአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ ቀሪው 2 ሺህ 177.1 ኩንታል ደግሞ መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች የተመደበ መሆኑን ከአመዝኤ የዕርዳታ ኘሮግራሞች አፈፃፀም ክትትል መምሪያ የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡

ለየክልሎች የሚደረገው የዕርዳታ አመዳደብም በየክልሎቹ እንደተከሰተው የተፈጥሮ አደጋ ስፋት ፣ ጥልቀት እና በአደጋው ጉዳት እንደደረሰበት ህዝብ መጠን የሚለያይ ነው፡፡ በዚሁ መሠት ለህዳር ወር ከተመደበው ጠቅላላ 100 ሺህ 877.1 የምግብ ዕርዳታ ውስጥ ለመደበኛ ተረጂዎች የተመደበው 93 ሺህ 470.1 ኩንታል ሲሆን ከዚህ ውስጥ ለኦሮሚያ 73 ሺህ 572.1 ኩንታል ፣ ለአማራ 11 ሺህ 301 ኩንታል፣ ለሱማሌ 8 ሺህ 597 ኩንታል ተመድቧል፡፡ ቀሪው 7 ሺህ 407 ኩንታል ምግብ ደግሞ ለጎርፍ ተጎጂ ወገኖች የተመደበ ሲሆን ከዚሁ ውስጥ 6 ሺህ 847 ኩንታል ለደቡብ ህዝቦች

ቀሪው 560 ኩንታል ደግሞ ለድሬዳዋ የጎርፍ ተጎጂዎች የተመደበ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል።




ከዚህም ሌላ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ለሚገኙ የጎርፍ ተጎጂዎች ከተመደበው 6ሺህ 847 ኩንታል የምግብ ዕርዳታ ውስጥ 3 ሺህ 987 ኩንታል በደቡብ ኦሞ ዞን ለሚገኙ የጎርፍ ተጎጂዎች የተመደበ ቀሪው 2 ሺህ 860 ኩንታል ደግሞ በተለያዩ ሌሎች ወረዳዎች በጎርፍና የመሬት መንሸራተት ጉዳት ለደረሰባቸው ወገኖች የተመደበ መሆኑን ከዕርዳታ ፕሮግራሞች አፈጻጸም ክትትል መምሪያ የተገኘው መረጃ ያመለክታል።

በተለያዩ ክልሎች በደረሱ የተፈጥሮ አደጋዎች ሳቢያ የአስቸኳይ ጊዜ ዕርዳታ ለሚያስፈልጋቸው ወገኖች ለህዳር ወር በጠቅላላው 100 ሺህ 877.1 ኩንታል የምግብ ዕርዳታ ተመድቧል።

## በትራንስፖርትና በመንገድ ብልሽት ምክንያት የዘገየው ዕርዳታ መከፋፈል ጀመረ

በሱማሌ ክልል ባለፈው ጥቅምት ወር 1999 ዓ.ም በጣለው ዝናብ ሳቢያ የዋቢ ሸበሌ ወንዝ ሞልቶ በመፍሰሱ ባስከተለው የጎርፍ አደጋ የተጎዱ ወገኖቻችንን ለመርዳት ከፌዴራል አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ ድሬዳዋ ማዕከላዊ መጋዘን ተጓጉዞ በመንገድ ብልሽት ሣቢያ ለተረጂዎች ሳይደርስ የዘገየው የምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ዕርዳታዎች መከፋፈል ጀምረዋል።

የፌዴራል አደጋ መከላልና ዝግጁነት ኤጀንሲ የሕዝብ ግንኙት ቡድን በጎዴ ዞን ቆላፎና ምዕራብ ጎዴ ወረዳዎች ተገቃቶ እንደተመለከተው ፣ የምግብ ዕርዳታ ፣ የቤት ቁሳቁስ የለሊት አልባሳትና የወባ መከላከያ አጎበር በቀላፎ ወረዳ አርጎዳዳ በተባለ ቀበሌ የማከፋፈል ሥራ ተጀምሯል።

አቶ አሊ አብዱለሂ የቀላፎ ወረዳ አስተዳዳሪ ለቡድኑ እንደገለጹት በወረዳው ከጥቅምት 9 እስከ 26 ቀን 1999 ዓ.ም በተከታታይ ሳያቋርጥ የጣለው ከፍተኛ ዝናብ ለጎርፍ አደጋው መባባስ አስተዋጽዖ በማድረጉ የዋቢሸበሌ ወንዝ ሞልቶ የጎርፍ መጥለቅለቅ አደጋ በማስከተል የተጎዱ ወገኖችን ለመርዳት መንግሥት ዕርዳታ ቢልክም ፣ በመንገድ ብልሽት ሳቢያ ዕርዳታው እስከ ህዳር ወር ዘግይቷል በአሁኑ ጊዜ መንገዱ በመድረቅ ላይ በመሆኑ ምግብ ነክ ያልሆኑ ዕርዳታዎችና ምግብ በመከፋፈል ላይ ነው።

በአሁኑ ጊዜ ለቀላፎ ወረዳ ከተላኩት 23 ተሽከርካሪዎች ውስጥ 8 ያህል ተሽከርካሪዎች ቀላፎ መድረሳቸውን የገለጹት አስተዳዳሪው የደረሰው እህል በጭቃ ምክንያት እንዳይዘገይ ወደየቀበሌዎች በጋማ ከብት ለማድረስ ጥረት ይደረጋል ብለዋል።

ቀሪዎቹን 15 ተሽከርካሪዎች ከጭቃ ለማውጣት በዶዘር የታገዘ እንቅስቃሴ በመደረግ ላይ መሆኑን የገለጹት አቶ አሊ አብዱላሂ የዋቤ ሸበሌ ወንዝ ሙላት ወደ ቀላፎ ከተማ ሙሉ በሙሉ በመግለበጡ ሳቢያ የተበላሹ የከተማዋን መንገዶች ከየቤቱና ሽንት ቤቱ የወጣውን ቆሻሻ በማፅዳት በጤና

በሱማሌ ክልል ባለፈው ጥቅምት ወር 1999 ዓ.ም በጣለው ዝናብ ሳቢያ የዋቢ ሸበሌ ወንዝ ሞልቶ በመፍሰሱ ባስከተለው የጎርፍ አደጋ የተጎዱ ወገኖቻችንን ለመርዳት ከፌዴራል አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ ድሬዳዋ ማዕከላዊ መጋዘን ተጓጉዞ በመንገድ ብለሽት ሣቢያ ለተረጂዎች ሳይደርስ የዘገየው የምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ዕርዳታዎች መከፋፈል ጀምረዋል።

ላይ የሚከሰተውን ችግር ለመቅረፍም ጥረት በመደረግ ላይ መሆኑን አስታውቀዋል።

በምዕራብ ጎዴ ወረዳ በፌዴራልና ከክልል የተገኘ የሰው መድሀኒት ፣ 400 ካርቶን



ብስኩት 400 ያህል ብርድ ልብስ ፣ 3 ጥቅል ኘላስቲክ ሸት እንደሁም አጎበር የተከፋፈለ ሲሆን የምግብ ዕርዳታና ሌሎች የቤት ቁሳቁስ ዕርዳታዎችን ለማድረስ ሳይቻል ቢቆይም ከህዳር 9 ቀን 1999 ዓ.ም ጀምሮ ዕርዳታውን ለማድረስ ጥረት በመደረግ ላይ መሆኑን አቶ ጣሂር አብዱ አብዱላሂ የጎዴ ዞን የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ጽ/ቤት ኃላፊ ገልጽዋል።

በጎዴ ዞን በተከሰተው ጎርፍ በከፍተኛ ደረጃ የተጠቃው አካባቢ በተሽከርካሪ መግባት ስለማይቻል ዕርዳታውን በሄሊኮኘተር ለማድረስ መንግሥት ከፍተኛ ጥረት በማድረግ ላይ መሆኑን አቶ ነዲር አዴን ሀሰን የጎዴ ዞን አስተዳደር ለቡድኑ ገልጽዋል። በጎዴ ዞን የሚገኙት 6 ወረዳዎች የዋቢ ሸበሌ ወንዝን ተከትለው የሚኙ በመሆናቸው በባሌ ደጋማ ቦታዎች ከፍተኛ ዝናብ ሲጥል ለጎርፍ አደጋ የሚጋለጡ በመሆናቸው በዘንድሮው የጎርፍ አደጋ 80 ሰው መሞቱን እና ከ300 ሺ ህ ሕዝብ በላይ መፈናቀሉን ከዞኑ የተገኘው መረጃ ያመለክታል።

## በሱማሌ ክልል ለጎርፍ አደጋ ተጎጂዎች የዓለም ምግብ ኘሮግራም ሄሊኮኘተሮች ዕርዳታ በማቅረብ ላይ ይገኛሉ

በሱማሌ ክልል ጎዴ ዞን በዋቢ ሸበሌ ወንዝ ሙላት ሳቢያ በቅርቡ በደረሰው የጎርፍ መጥለቅለቅ አደጋ ተጎጂ ለሆኑ ወገኖች የምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ዕርዳታ ቁሳቁሶችን በማድረስ እንዲያግዙ በተመድ አማካይነት በዓለም ምግብ ኘሮግራም አስፈፃሚነት ወደ ኢትዮጵያ የመጡት ሁለት ሄሊኮኘተሮች የምግብና የቁሳቁስ ዕርዳታ ለአደጋው ተጎጂዎች እያቀረቡ ነው።

በኢትዮጵያ የዓለም ምግብ ኘሮግራም ሎጀስቲክስ ክፍል ኃላፊ ዮሀንስ ካትሳሮስ እና በዓለም ምግብ ኘሮግራም የአቪየሽን መኮንንን እና በኢትዮጵያ ለሚደረገው ተልዕኮ የመጣው ቡድን መሪ የሆኑት ኤይነር ስሺጀልበርግ ሔሊኮኘተሮቹ ህደር 19 ቀን 1999 ዓ.ም ወደ ጎዴ ለመጓዝ አዲስ አበባ ባረፉበት ወቅት ስለተልዕኮው በሠጡት መግለጫ እንደተናገሩት ሁለቱ ሄሊኮኘተሮች ከህዳር 20 ቀን 1999 ዓ.ም ጀምሮ ለሁለት ሳምንት በጎዴ በሚያደርጉት ቆይታ በተሽከርካሪ ሊደረስባቸው በማይችሉ ሙስታሂል እና ምሥራቅ ኢሚ ወረዳዎች እንዲሁም አጎራባች አካባቢዎች ለሚገኙ የጎርፍ ተጎጂ ወገኖች በአመዝኤ፣ በዓለም ምግብ ኘሮግራምና በሌሎች የረድዔት ድርጅቶች ጎዴ ድረስ የተጓጓዘውን የምግብና

ቁሳቁስ ዕርዳታ በማድረስ ከፍተኛ ዕገዛ ያደርጋሉ፡፡ እንደ ኃላፊዎቹ ገለፃ ሄሊኮፕሮቹ በቀን ውስጥ ሦስት ጊዜ በሚያደርጉት ምልልስ 180 ኩንታል የምግብና የቁሳቁስ ዕርዳታ ለተጎጂዎች የማድረስ አቅም አላቸው፡፡

ኤጀንሲ ዕርዳታ ማሰባሰብና ሕዝብ ግንኙነት አገልግሎት መምሪያ ኃላፊ አቶ ጌታቸው ተስፋዬ እንደተናገሩት የዓለም ምግብ ኘሮግራም ለጎርፍ ተጎጂዎች የምግብና ቁሳቁስ ዕርዳታ ከማቅረብ በተጨማሪ በቦታ ርቀትና የመንገዶች በአደጋው መውደም ሳቢያ

> በሱማሌ ክልል ጎዴ ዞን በዋቢ ሸበሌ ወንዝ ሙላት ሳቢያ በቅርቡ በደረሰው የጎርፍ መጥለቅለቅ አደጋ ተጎጂ ለሆኑ ወገኖች የምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ዕርዳታ ቁሳቁሶችን በማድረስ እንዲያግዙ በተመድ አማካይነት በዓለም ምግብ ኘሮግራም አስፈፃሚነት ወደ ኢትዮጵያ የመጡት ሁለት ሄሊኮፕተሮች የምግብና የቁሳቁስ ዕርዳታ ለአደጋው ተጎጂዎች እያቀረቡ ነው፡፡




ለሄሊኮፕተሮቹ እና አስር ለሚሆኑ የበረራ እና ሎጀስቲክስ ክትትል ቡድን አባላት የሚያስፈልገውን ወጪ ሙሉ በሙሉ የሚሸፍነው የዓለም ምግብ ኘሮግራም እንደሆነም ለመረዳት ተችሏል፡፡

ሄሊኮፕተሮቹን ወደ አዲስ አበባ ይዞ የመጣው ቡድን አዲስ አበባ ቦሌ ዓለም አቀፍ አይሮኘላን ማረፊያ ሲደርስ አቀባበል ያደረጉላቸው የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ለተጎጂዎች በተሽከርካሪ ዕርዳታ ማድረስ አስቸጋሪ በሆነባቸው ቦታዎች ዕርዳታ ለማድረስ የዚህ ዓይነት እገዛ ማድረጉን የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ በከፍተኛ አድንቆት የሚመለከተው መሆኑን አመልክተው ይኸ በአይነቱ የመጀመሪያ የሆነው የዓለም ምግብ ኘሮግራም ድጋፍ ለወደፊቱም መሰል አደጋዎች ካጋጠሙ በተጠናከረ መልኩ እንደሚቀጥል ያላቸውን እምነት ገልፀዋል፡፡

## በመኸር አምራች እና በአርብቶ አደሩ አካባቢዎች የምግብ ዋስትናን ሁኔታ የሚያጠኑ ቡድኖች ተሠማርተዋል

መኸር አምራች በሆኑ የሀገሪቱ አካባቢዎች የቅድመ መኸር አዝመራ ሁኔታንና በአርብቶ አደር አካባቢዎች የሚታየውን የምግብ ዋስትና ሁኔታ የሚገመግሙ በፌዴራል አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ አስተባባሪነት ከኤጀንሲው፣ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የፌዴራልና የክልል መ/ቤቶች፣ መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶችና የረድኤት ድርጅቶችና የተመድ ልዩ ልዩ አካላት የተውጣጡ ባለሙያዎችን ያካተቱ 19 የመስክ አጥኚ ቡድኖች ከህዳር 9 ቀን 1999 ዓ.ም ጀምሮ ወደ ተለያዩ ክልሎች ተሠማርተው አስፈላጊውን ጥናት በማካሄድ ላይ ይገኛሉ፡፡

በዚህ ጥናት ተሳታፊ ለሚሆኑ አካላት ህዳር 8 ቀን 1999 ዓ.ም በአመዝኤ የመሰብሰቢያ አዳራሽ በተደረገው ገለፃ እና ውይይት ላይ እንደተገለጸው በሁሉም ክልሎች የሚሠማሩት 19 አጥኚ ቡድኖች በትግራይ ፣ አማራ ፣ ኦሮሚያ እና ደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልሎች በሚገኙ 34 መኸር አምራች ዞኖች እንዲሁም ቤንሻንጉል ጉሙዝ ፣ ጋምቤላ ፣ ሐረሪ እና ድ ደዋ አስተዳደር ፣ በሱማሌ እና አፋር ክልሎችና እንዲሁም ኦሮሚያ ክልል ቦረና ዞንን ጨምሮ 15

አርብቶ አደር ዞኖች በመሠማራት ጥናቱን ያካሂዳሉ።



በዚሁ በመስክ ጥናቱ ዙሪያ በተካሄደው ውይይት ላይ እንደተመለከተው የጥናቱ ዓላማ የመኸር አዝመራ ውጤትን እና በመኸር አምራቹ አካባቢ የምግብ ዋስትና ላይ የሚኖረውን አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ተፅዕኖ ተዘዋውሮ በመስክ በማጥናት እንዲሁም በአርብቶ አደሩ አካባቢዎች የእንስሳት ፣ የግጦሽ ፣ የውሃ እና ምግብ ዋስትና ሁኔታዎችን በመገምገም፣ በመጪው የፈረንጆች 2007 ዓ.ም የአስቸኳይ ጊዜ ዕርዳታ የሚያስፈልጋቸው አካባቢዎች የሚኖሩ ከሆነ ለይቶ በማቅረብ ዕርዳታው ለምን ያህል ህዝብ እና ለምን ያህል ጊዜ እንደሚያስፈልግ መጠቆም እና ምግብ ነክ ያልሆኑ ዕርዳታ ፍላጎቶችንም በጥናቱ ውስጥ ማካተት ነው።

አጥኚ ቡድኖቹ ጥናታቸውን በምን አይነት ዘዴ ማካሄድ እንደሚገባቸው ፣ በጥናቱ ወቅት ትኩረት ሊሠጧቸው በሚገቡ ጉዳዮች ፣ ወደ ዞንና ወረዳዎች ከመድረሳቸው በፊት ምን ማድረግ እንደሚገባቸው ፣ በጥናቱ አካባቢዎች ማነጋገር የሚገባቸውን የህብረተሰቡን ክፍሎች ፣ ለጥናቱ የሚጠቀሚቸውን መሣሪያዎችና የአጠናን ዘዴዎች እንዲሁም ሌሎች ተዛማጅ ሁኔታዎች አስመልክቶ በዚሁ ስብሰባ ላይ ሠፋ ያለ ማብራሪያ እና ውይይት ተካሂዷል።

ከሱማሌ ክልል በስተቀር ወደ ሌሎች ክልሎች የተሰማሩት አጥኚ ቡድኖች ከህዳር 9 ቀን 1999 ዓ.ም ጀምሮ ወደየተመደቡባቸው ዞኖች የተሰማሩ ሲሆን በሱማሌ ክልል መኸር አምራች እና አርብቶ አደር አካባቢዎች ጥናታቸውን የሚያካሔዱት ደግሞ ከህዳር 15 ቀን ጀምሮ ወደየተመደቡበት አካባቢ ተንቀሳቅሰው ለ3 ሳምንታት የሚቆየውን የመስክ ጥናት በማካሔድ ላይ የሚገኙ መሆኑ ታውቋል። ሁሉም ቡድኖች በጥናታቸው የሚደርሱበትን ውጤት ታህሳስ 5 ቀን 1999 ዓ.ም በክልል ደረጃ በማጠናቀር ማዕከል ላይ በሚያቀርቡት ሪፖርት ያሳውቃሉ ተብሎ ይጠበቃል።

*መኸር አምራች በሆኑ የሀገሪቱ አካባቢዎች የቅድመ መኸር አዝመራ ሁኔታንና በአርብቶ አደር አካባቢዎች የሚታየውን የምግብ ዋስትና ሁኔታ የሚገመግሙ በፌዴራል አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ አስተባባሪነት ከኤጀንሲው፣ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የፌዴራልና የክልል መ/ቤቶች፣ መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶችና የረድኤት ድርጅቶችና የተመድ ልዩ ልዩ አካላት የተውጣጡ ባለሙያዎችን ያካተቱ 19 የመስክ አጥኚ ቡድኖች ከህዳር 9 ቀን 1999 ዓ.ም ጀምሮ ወደ ተለያዩ ክልሎች ተሠማርው አስፈላጊውን ጥናት በማካሄድ ላይ ይገኛሉ።*